# በምርጫ ዋዜማ አማራጭን እንጂ ጫጫታን አንሻም !! (፪)

ዮናስ 12-04-14

በዚህ ክፍል፣ በክፍል አንድ የተመለከትነውን ምርጫ 2007 የተመለከተ እና ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከአማራጭ ይልቅ ጫጫታ ሱስ ስለሆነባቸው ፓርቲዎቻችን መመልከታችንን እንቀጥላለን። በዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ገዥ የነበረ ፓርቲ ተቃዋሚ፣ ተቃዋሚ የነበረውም ገዢ የመሆኑ ጉዳይ የተለመደና የሚጠበቅ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስልጣን ሽግግር ያለአንዳች ችግርና ቀውስ በሰላማዊ መንገድ የሚፈፀም ከመሆኑም ባሻገር ህብረተሰቡ በሚመራባቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥን የሚያስከትል አይሆንም፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች "ታማኝ ተቃዋሚ (ሎያል ኦፖዚሽን)" በሚል ስያሜ የሚታወቁ የራሳቸው የተለየ ፓሊሲ ከማቅረብ ባሻገር ስርዓቱን የመናድ ሃሳብና ተግባር የሌላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ እንደነ *አንድነት፣ መኢአድ፣ ሰማያዊ* እና የመሳሰሉት በህግ የሚመሩትንና ህገመንግሥታዊ ስርዓቱን አክብረው፣ ህጉ በፈቀደው ሜዳ ላይ ለመጫወት ፈቃደኛ የሆኑትን ፓርቲዎች "ቅልብ እና ተለጣፊ"፤ አመፀኞችንና ህግና ህገወጥነተን ቀላቅለው የሚጠቀሙትን ደግሞ "ህዝባዊና ሃገራዊ" እያሉ በማሸማቀቅና በማሞገሥ አይሆንም፡፡

በአገራችን ከላይ የተጠቀሰውን አወንታዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ጠንካራ ፓርቲዎች እንዳይፈጠሩ እንቅፋት የሚሆኑ ከኋላቀርነታችን ጋር የተያያዙቱ በርካታ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው በምርጫ ዋዜማ ላይ ብቻ ብቅ ብለው የሚጠፉ የመስቀል ወፍ ፓርቲዎች የሚሰጡት አፍራሽ መግለጫና የአራጋቢ ጋዜጦችም (ልሳኖቻቸው ላለማለት ነው) በሬ ወለደ፣ ሰማይ ተቀደደ . . . ዜናና ዘገባዎቻቸው አሉታዊ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑ በገሀድ እየታየ ነው፡፡

ተቃዋሚ መሆን ማለት መናድ፣ ማፍረስ፣ በተገኘው አጋጣሚና ባመቸ ስልት ሁሉ በመጠቀም ማደናቀፍ ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ እንዲፈጠር እነዚህ ሃይሎች አሁንም እየሰሩ ስለመሆናቸው ከመግቢያው ጀምሮ ባየናቸው ሁነቶች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በክፍል አንድ የተዘረዘሩት ነባራዊ ችግሮች እንደኛ ባሉ አገሮች ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊኖሩ እንደማይችሉ ወይም የዴሞክራሲ ስርዓት ሊገነባ እንደማይችል

የሚያመላክቱ ሳይሆኑ ይልቁንም የነዚህ ነባራዊ ችግሮች መኖር ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመፍጠርና የዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት ከፍተኛ ትግልና ጥረት፣ ከፍተኛ ጥንቃቄና ብቃት ያለው የአፈፃፀም ስልት የሚጠይቅና ለዚህም የፖርቲዎችን የጋራ ምክር ቤት ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ፣ ፍንጭ የሚሰጥ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ ቅዠት መሰል ፖለቲካ ተምረው ቢያንስ በአማራጭ ፖለቲካ መድረኩ ላይ ይመጣሉ ብለን ስንጠብቃቸው የነበሩት ፓርቲዎች ቀድሞ ነገር ስማቸውን ለውጠው ቢመጡም ከመንጫጫት የዘለለ አማራጫቸውን እስካሁን አላሳዩንም። በውስጣቸውም እዚህ ግባ የሚባል ለውጥም ባለማድረጋቸው ከዚያው፣ ከቅዠት መውጣት ተስኗቸው አማራጭ ፖሊሲዎችን ለሚጠብቀው ህዝብ የሰላማዊ ሰልፍ፣ የህዝባዊ ስብሰባ፣ የሻማ ማብራት እና አሁን ደግሞ ቢያንስ ህጋዊ አመራር መሆኑ ጥያቄ ውስጥ ባለበት ሁኔታ አንድነት የተሰኘው ፓርቲ የፌስ ቡክ አብዮትን የምርጫ 2007 አማራጭ ማድረጉን በይፋ ነግሮናል። የተሻለ አማራጭ ፖሊሲ ጥያቄዎች እየቀረቡላቸው ሳለ መንጫጫትን ምሳና ራት ማድረጋቸው ስለ እነርሱ ሳይሆን ስለ ሃገሪቱ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንደ ዜጋ ያሳዝነናል፡፡ ከቅንጅትና ህብረት የተራረፉትም ሆነ የቅንጅትና ህብረት አካል ፓርቲ የነበሩትን መድረክ፣ አንድነት፣ ሰማያዊ፣ መኢአድ እና ወዘተ ፓርቲዎች ያሳለፏቸውን ፖለቲካዊ ተሳትፎ (በቆይታ ዘመናቸው ቢለያዩም) ስንገመግማቸው ተመሳሳይና በአንድ ቦይ ላይ ሲፈሱ የነበሩ መሆናቸውን እንዴትም ሆኖ ማስተባበል አይቻልም፡፡

እነዚህን ፓርቲዎች ወደኋላ መለስ ብለን ብናስታውስ ሁሉም በቤታቸው ዴሞክራሲን ማስፈን ተስኗቸው እርስ በርሳቸው ሲባሉና ሲቆራቆዙ በኋላም ገገርው ፓርቲ ላይ ሲያላክኩ መስማትም ሆነ ማየት ለማንም አዲስ አይደለም፡፡ በሌላ በኩልም የተለያዩ አማራጮችን በምንሻ ሰዓት የ"አንወዳደርም"ን የዜሮ ድምር ፖለቲካ እንደ ተሻለ አማራጭ በመውሰድ አቋማቸውም ይመሳሰላሉ፡፡ እነዚህ ኪራይ ሰብሳቢ ሃይሎች በሃይማኖት አስባብና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የሚፈጥሯቸውን ሁከቶችም እንደጥሩ አጋጣሚ በመውሰድ በሰላማዊ ሰልፍ ስም ከአክራሪ ሃይሎች ጋር በሚፈጽሟቸው ጋብቻዎችም ይገለጻሉ፡፡ ምን ይህ ብቻ፣ የጠለፋ ጋብቻ፣ ያልተቀደሰና ከፖለቲካዊ መርህ ብቻ ሳይሆን ከህግ ውጪ መሆኑንም እየተናገርንና እነሱም እያወቁት ጆሮአቸውን ደፍነው በዚሁ ባልተቀደሰው ጋብቻ ላይ

የበላይነቱን ለመያዝ በሚያደርጉት የእርስ በእርስ መናቆርም ይገለጻሉ፡፡ በህግ የበላይነት ላይ ሲያላግጡና ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ለአደጋ ለማጋለጥ በመፍጨርጨር ላይ ሳሉ የተያዙ ህገወጥ አካላትን ሁሉ ልክ አንደነ ቅንጅት የፓርቲያቸው አባል እንደሆኑ በማስወራትና ለተመሳሳይ ዓለማ በተሰለፉ ፕሬሶች አማካይነት በማራገብም አንድነታቸውን ስለመግለጣቸውን ጨምሮ በብዙ ማሳያዎች ማስታወስ ይቻላል፡፡ መሪና ተመሪው ሳይለዩም በነዚህ አራጋቢ ፕሬሶቻቸውና በማህበራዊ ሚዲያዎች ሲጠላለዙና እርስ በእርሳቸው መግባባት ተስኗቸው (ቢያንስ ገመናቸውን እንኳ መሸፈን አቅቷቸው) አደባባይ የወጡባቸውን በርካታ ሁነቶችም በማስታወስ አንዳቸው ከአንዳቸው የማይሻሉና አድሮ ቃሪያ መሆናቸውንም ማስታወስ አይከብድም፡፡ የዲሞክራሲ ተቋማት በሚባሉት የመንግስት መዋቅሮች ላይም ዘመቻ በመክፈት አማራጭ የጠየቃቸውን ህዝብ በተቋማቱ ላይ አመኔታ የማሳጣትን አማራጭም በተደጋጋሚ መሞከራቸውን በከሸፉት ሙከራዎችም ማስታወስ ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ ግን እነዚህ ሁሉ ሙከራዎቻቸው ቢከሽፉም ቢያንስ እነርሱ እንደሚሹት የስልጣን ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ የሚያሳስበን አማራጭ ማጣታችንና የሃገሪቱን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ወደ ኋላ እንዳይወስዱት መተማመኛ ማጣታችን ነው፡፡ ስጋታችን ደግሞ ዝም ብሎ ሳይሆን ጠንከር ያሉ እና ከላይ ለተመለከቱት መመሳሰላቸው ሁነኛ ማሳያ የሚሆኑ አስረጂዎች ያሉን መሆኑ ነው፡፡

ቀጥለን በክፍል አንድ ላይ አንስተነው፣ ነገር ግን ሳንቃጨው በይደር ወዳቆየነው ጉዳያችን እንመለስ።

የመድበለ ፓርቲን ንድፈ ሃሳባዊና  ተግባራዊ ሃቆች ማጠየቂያ አድርገን የሃገራችንን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአማራጭ ይልቅ የመንጫጫት ፖለቲካቸውን ወደኋላ 10 አመት ተመልሰን በክፍል አንድ ትርክታችን አይተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ በክፍል አንድ ማጠየቂያዎቻችን በተመሳሳይ የተቃዋሚዎቹን ምርጫ 2007 ታሳቢ ያደረገ የአማራጭ ሳይሆን የመንጫጫት ፖለቲካ እናጠይቃለን። ይህን ጉዳይ በስፋት የምናየውና የምንወተውተው ከአማራጭ ይልቅ መንጫጫትን ስራ ስላደረጉብን እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱ ላይ ጥላ ስለጣሉብን እንጂ ተራ ጥላቻ ተደርጎብን ወይም ደግሞ እንደለመዱትም ትርክታችን የካድሬ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይገባ ከወዲሁ እናሳስባለን።

በክፍል አንድ የተመለከተውና ከብዙ በጥቂቱ የተተረከው ተቃዋሚዎቹን የተመለከቱ ሃቆች ባሉበት አግባብ ላይ ስጋታችን እየጨመረብን እንዲመጣ ደግሞ አሁንም ከዚሁ ሳይወጡ ከላይ በተመከለቱት ባህሪያቸው መቀጠላቸውና ይልቁንም መገጫጨቱ እየባሰባቸው መሄዱ በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመዋሃድና መጣመር ሱሳቸውም ቢሆን ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዙር ቀርቶ ለአንድ ሳምንትም ሳይወስዳቸው ከመንገድ ያስቀራቸው መሆኑን ያጠየቅንባቸው ከላይ የተመለከቱ ልምዶች ባሉበት ሁኔታ አሁንም በዚያውና በመንጫጫት መንገድ ለመጓዝ መሻታቸው ምክንያት ሆኖናል፣ 5ኛው ሃገር አቀፍ ምርጫ በተቃረበበትና አማራጭ ከማቅረብ በዘለለ በምርጫ ስራ ላይ ጊዜያቸውን ማዋል በሚገባቸው ሠዓት ላይ ሆነው፡፡

ምንም እንኳ ከላይ በተመለከተው አግባብ መድረኩም እንደ መድረክ አባል ፓርቲዎቹን በዴሞክራሲያዊ አግባብ ይዞ መዝለቅ የተሳነው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድነትም ከመድረኩ በወጣባቸው እና ከመኢአድ ጋር ሊያደርግ የነበረው ውህደት የከሸፈባቸው ጸረ ዴሞክራሲያዊ አግባቦች እንደተጠበቁ  ሆነው፣ ቢያንስ በመርህ ደረጃ ሰማያዊ የተሰኘው ፓርቲ የመድረኩ አባል እንዲሆን በተጠየቀ ወቅት የሰጠውን ‹‹ በጥምረትና በጋራ ሊያሰራ የሚችል ነባራዊ ሁኔታና አመራር የሌለ መሆኑን›› የጠቀሰበትን አግባብ እያስታወስን አሁንና ሰሞኑን "የዘጠኝ ፓርቲዎች ስብስብ ›› በማለት ያቋቋመው  ጥምረት ለምን አላማ እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡

የመጀመሪያውና ለእውነት የቀረበው ግምት በጠለፋ ያደረጋቸውን ሰልፎች መነሻ አድርጎ እራሱን  ያበዛበት አማራጭ አሁን ዝግ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ በአደባባይ ጩኸቱ የዜሮ ድምር ጫወታው  ያጣውን ገንዘብና የሰዎች መዋጮ ከእነዚህ ፓርቲዎች ለማካካስ ሲሆን፣ ከሁሉ የሚልቀው ደግሞ የአማራጩን ጉዳይ ለመንጫጫት የቁመራ አሰላለፍ ማመቻመች ነው፡፡ ይህ ሀቅ ስለመሆኑም ከሰሞኑ የሆነውን በማጤን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከሰላማዊ ሰልፍና ህዝባዊ መድረኮች ጋር ተያይዞ ፓርቲዎች ሊከተሉት የሚገባው ህጋዊ መንገዶች መኖራቸው እሙን ነው፡፡ ከነዚህ መንገዶችም የመጀመሪያው ህጋዊ መሆንን የሚጠይቀውና በየትኛውም መለኪያ ለድርድር የማይቀርበው የህጋዊነት ጥያቄ ነው ፡፡ ዘጠኙ ፓርቲዎች በጥምረት ለመስራት መሰባሰባቸው በራሱ መብትና በመርህ ደረጃም ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓቱ መጎልበት ወሳኝ ድርሻ ያለው መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ግን

ደግሞ ስብስቡ ፓርቲዎችን ለማስተዳደር ስልጣን ከተሰጠው አካል እውቅና ማግኘትና ለባለስልጣኑ ህግጋትም መገዛትን እንደሚጠይቅ አያጠራጥርም፡፡ በዚህ አግባብ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የዘጠኙ ፓርቲዎች ስብስብ  የእውቅና ሰርተፊኬት ባላገኘበት ሁኔታ (ያላገኘውም የምርጫ ቦርዱን ህግ ባልጠበቀ መንገድ መመስረታቸው መሆኑ በቦርዱ ይፋ ሆኗል፡፡)  በዘጠኙ ፓርዎች ስም ሰላማዊ ሰልፍ መጥራታቸው ነው ህገወጥነቱ። ያለቦርዱ እውቅና እንደ ጥምር ፓርቲ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የሚቻል ነው እንኳ  ብለን ብንወስድ ገና እንኳን እንደ ዘጠኝ በነጠላም በሀሉት እግራቸው ያልቆሙ ፓርቲዎች፣ አንዳቸው ከአንዳቸው አለን በሚሏት ፕሮግራምም እንኳ ለየቅል በሆኑበት አግባብ፣ የሚበዙት ክልላዊ ፓርቲዎች መሆናቸውም በሚታወቅበት አግባብ፣ አዲስ ሊያደርጉ በነበረው ሰልፍ ሊያነሱ የታሰበው አጀንዳ ምንድን ነበር? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ሲሆን መልሱም የተጣመዱበትን፣ ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶች ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡ (በነገራችን ላይ በክፍል አንድ በተመለከተው የየፓርቲዎቹ የትውስት ቅኝታችን ህገወጥነትን አስበው የሚሰሩትና ከተከለከልን የምህዳር መጥበብ የማትረፍ ስትራቴጂም እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡)

ይኸው በዘጠኙ ፓርቲዎች በኩል፣ ህገወጥም ሆነው እንኳን፣ እየሰማን ያለነው ይህንኑ ነው፡፡ ህዳር 7/2007 "ዘጠኙ. . .።  የተባሉትና በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የዘጠኝነትን እውቅና  ያላገኙት ፓርቲዎች የጠሩት ሰልፍ፣ አስቀድሞ ነገር ሰልፉ ሳይሆን እነርሱ ህገወጥ ናቸውና እንደ ዘጠኝ የሌላቸውን ማህተምና ሌሎች ፓርቲያዊ ወይም ጥምረታዊ የጋራ ሰነዶች  መነሻ በማድረግ የሚመለከተው አካል ሰልፍ ቀርቶ ሌላም ቢነፍጋቸውና የህግ ጥያቄ ቢያነሳባቸው ተገቢ ቢሆንም፣ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መከልከላቸውን አስቀድሞም የሚያውቁት ነበርና *በደህንነትና በመንግስት ካድሬዎች ሰልፋችን ታገደ* ሲሉ ቢያወሩ ስትራቴጂ መሆኑን ህዝቡ ሊያጤነው ይገባል፣ ያውቀዋል፡፡ ምክንያቱም እንኳንስ ህገወጥ ተሁኖ፣ ህጋዊ ተሆኖም (ታዳጊ እንደመሆናችን አስቀድሞ ይጠበቃልና) ከሚኖሩ ችግሮችም ጋር አማራጭን እንጂ መንጫጩትን ስለማያተርፈን አንሻም። *መንጫጫታቸውን ትተን አሁን ማድረግ የሚገባን ኢህአዴግ ስለሚፈራን ነው፣ ምርጫው ላይ እንደምንረታው ስላወቀ ነው . . .*  ወዘተ በማለት ከመቆለል ይልቅ በየትኛው ፕሮግራም ገዥውን ፓርቲ ሊረቱት እንደሚችሉና በየትኛው አማላይ ፖሊሲያቸው ኢህአዴግ እንደፈራቸው እንዲያሳውቁን መጠየቅ ነው፡፡

አንድነት የተሰኘውንም ፓርቲ ሰሞነኛ ሁናቴ ስናይ በመጣበት መንገድ መቀጠሉንና ከዘጠኙ ፓርቲዎች ያልተለየ መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ አንድነት እንደ ፓርቲ ሆኖ ያደረገው የአመራር ለውጥ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ህግጋትም ሆነ ሳይንስ ይቅርና የራሱንም የመተዳደሪያ ደንብ የጣሰና ስለመጣሱም የነበረው አመራርም ሆነ በርካታ አባላቱ እንደማይቀበሉት ለምርጫ ቦርድ በደብዳቤ ማሳወቃቸውን፤ ይልቁንም ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አንድነት የራሱን ህግና መተዳደሪያ ደንብ መጣሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤ ሳይጠራ (ሲጠራም ምርጫ ቦርድ ማወቅና ወኪሉም መኖር ነበረበትና ይህ ሳይሆን) ያደረገው ለውጥ በራሱ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ህገ-ወጥም በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው ቦርዱ ይፋ ማድረጉን እያወቅን፣ ከሰሞኑ በቀጣዩ ምርጫ ስለመሳተፉ መግለጫ የመስጠቱ ጉዳይ ነው አሳፋሪውና ኪሳራው፡፡ በቀጣዩ ምርጫ መሳተፉ በራሱ ተገቢና እሰየው የሚያስብል ቢሆንም እራሱን ሳያጠራ እና ወደ ህግ ሳይመጣ፤ ይህም ቀርቶ የሚሳተፍባቸውን አማራጮች ሊነግረን ሲገባው የሰለቸነውን መንጫጫት ‹‹የሚሊዮኖች ድምጽ፣ የህሊና እስረኞች" ጂኒ ቁልቋል እንደአማራጭ ይዞልን መምጣቱ በራሱ ያሳዝናልም፣ ያሳፍራልም፡፡

የመድረክንም ሰሞነኛ ሁናቴ ስናጤን ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በእርግጥ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ከዚህ ፈቀቅ እንደማይል/ያደረግ ከላይ በሚገባ ከትውስታው መገንዘብ ችለናል፡፡ ያም ሆኖ ግን በዚህ የምርጫ ዋዜማ ላይ ሆነን መድረኩ የአባል ፓርቲዎቹን መልቀቅና ነገም ምን ሊሆን እንደሚችል በማይታወቅበትና  አባል ፓርቲዎቹ እየተንገዳገዱ ባለበት በዚህ ሰዓት ላይ፤ ስለ ጉዳዩ ማጥራትና ቀጣይ አማራጮችን ነድፎና አባል ፓርቲዎቹ በጋራ የሚጣሉበትን ፖለቲካ ከመሻት ይልቁን ላለፉት 2 ዓመታት ከመድረኩ ርቀው የነበሩትን እና ስለመድረኩ ውስጣዊ ፈተናዎች በቅጡ መረጃ የሌላቸውን ሰው ስለ ዜሮ ድምር ፖለቲካው ሊቀመንበር አድርጎ በመሾም የተለመደውን መንጫጫት መጀመሩም ያሳዝናል፤ ያስፍራልም፡፡ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ የደቡቡን ፓርቲ እንደ ግል ንብረታቸው በአደራ ሰጥተው ወደውጭ የመሄዳቸውን ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ጉዳይ ትተን፤ አሁን እንደመጡ ቢያንስ ካለፉት ዓመታት የተሻሉ የአማራጭ ስትራቴጂዎችን ያመጡ ይሆናል ብለን ብንጠብቅም ልክ እንደ ምርጫ 97ቱ እና 2002ቱ ከላይ በተመለከተው አግባብ ገዢው ፓርቲ ላይ መንጫጫታቸውን በይፋ ጀምረዋል፡፡ ያመጡልን አዲስ ነገር ቢኖር ያኔ ስለዜሮ ድምር ጨዋታቸው ሲያወድሱት የነበረው ዲያስፖራ ዛሬ የተዋቸው እንደሆነ

እና ግን ደግሞ ለምን የተዋቸው እንደሆነ ከመመርመር ይልቅ የገዢ ፓርቲ ቁማር ነው ሲሉ የማላዘን ኋላ ቀር ፖለቲካ ብቻ ነው፡፡

ወደ መኢአደም ስንመጣ ያውና ተመሳሳይ ነው፡፡ "ጠቅላላ ጉባኤ አድርጌ አቶ አበባው መሃሪን የፓርቲው ሊቀመንበር አድርጌ ሾሜያለሁ" እንዳላለን ሁሉ እርሳቸውም እንደ ፓርቲ ሊቀመንበር በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ሲሰጡና በስማቸው በወጡ ደብዳቤዎች ፓርቲያቸውን ሲመሩ እንዳልነበር ሁሉ እነ ማሙሸት አማረንም "ሌቦች ናቸው" ሲሉ በይፋ ክስ መመስረታቸውን እና አንዳንድ አመራሮችንም ከሰው  እንዳላሳሰሩ ሁሉ፣ ከሰሞኑ ድንገት አቶ አበባው መሃሪ ሊቀመንበር እንዳልነበሩ እና ሊቀመንበር አቶ ሃይሉ ሻወል መሆናቸውን በመግለጽ አቶ ማሙሸት አማረ ከአቶ ሃይሉ ሻወል ላይ ስልጣን መረከባቸውን ሲነግሩን እንዴት ያለ አሳፋሪ እንደሚሆን አስባችሁታል? አማራጭ ማጣታችን ይቅር፣ መንጫጫታቸውንም እንለፈው ቢያንስ ፖለቲከኝነቱ ቀርቶ እድሜያቸው ከ20ዎቹ በዘለሉ ግለሰቦች የማይጠበቅ ጨዋታ ውስጥ ሆነው ስለምርጫና ምህዳር መጥበብ ሲያወጉን ከማፈር ውጪ ምን ማድረግ ይቻላል፡፡?

የመድረኩ ድርጅታዊ ህልውና ተንጠልጥሎ  ባለበት ወቅታዊ ሁኔታ  ስለ ራሱም ሳያውቅ የወጣቶች ክንፍ ስለማቋቋሙ ቢያወራን፣ አንድነቱም እውቅና በሌለው አመራሩ ግራ ቢያጋባን፣ ዘጠኙም ዘጠኝ ቦታ ነገ እንደማይሆኑ ዋስትና በሌለበት አግባብ፣ መኢአድም በመጣበት መንገድ የነማሙሸት አማረን የነገ እጣ ፈንታ (ግና የምርጫ ቦርዱን የተቀባይነት  ማግኘት/አለማግኘተ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ) እየገመትን ቀጣዩን ምርጫ ስናስበው ከአማራጭ ይልቅ መንጫጫቱ እንደሚበረታ ብንገምትም፣ የሚያሳዝነን መንጨጫቱ በተለይ በቤታቸው እንደሚሆን ከላይ በተመለከቱት ተጠየቆች ብንገነዘብምና ውጪያዊ ጉዳት ባያደርሱብንም ለሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚኖራቸውን የከፋና ከበፊቱ የባሰ ፋይዳ ስናስበው ነው፡፡

ባጠቃላይ፣ እነዚህ ወገኖች አሁን ያሉበት ቁመና ከላይ የተመለከትነውን ይመስላል፣ ይህን ይምሰሉ እንጂ አሁንም ጊዜ አላቸው፣ በመሆኑም (ድምፃዊት ኩኩ ሰብስቤ “ትንሽ ጊዜ ስጠኝ. . .” እንዳለችው ማለት ነው) እንዲያስቡበት ትንሽ ጊዜ/እድል እንስጣቸው፡፡ በእድሉ ካልተጠቀሙበትና ሊማሩበት ፈቃደኛ ካለሆኑልን ደግሞ ከዚህ ምርጫ በኋላ

ላንሰማቸውና አንቅረን እንተፋቸው ዘንዳ ስለሃገራችን የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከሚያሳስበን ዜጎች ሁሉ የሚጠበቅ ሃላፊነት ይሆናል፡፡ አበቃሁ።